# ወጣት የነብር ጣት
# ከሆነስ እንዴት?

**ከመስፍን ግርማ ኖርዌይ ኦስሎ ጁላይ 2012**

ይታደላል እንጂ አይታገሉም እንዲሉ ምንም አይነት ፍጥረት ተጠቦም ሆነ ቀምሮ ክፍለ ዓለሙን አገርን ዘርና ቀለሙን ቀየውን መርጦ ወደዚህች ዓለም የመጣ የለም። የሰማያዊው ሥነ-ፍጥረት ህግ ይህንን አይፈቅድለትምና።

እነማን ማን እንደሆኑ የገባቸውና የታደሉት ደግሞ ኢትዮጵያዊነት በኩራት ይቀበሉታል፤ እንደ አንዳንዶቹ ዛሬያውያኖች ዘመነኞች መሰረትና ማንነታቸውን ለቀው ባለፉበት በሄዱበት ቦታ ሁሉ እንደ ሃረግ ዛፍ አይንጠለጠሉም ከየት እንደመጡና ማንነታቸውን ያውቃሉና።

በርግጥ ኢትዮጵያዊነት ኩራት ነው። ዛሬ አለምን እንደ ውኃ ቦይ ወደፈለገችበት እየማሰች የምትመራዋ አሜሪካ ኮሎንቦስ እንኳን ሳያገኛት አውሮፓ በጨለማው ዘመን የእርስ በርስ ጦርነትና ድንቁርና ሲደናበሩ የኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ግን በነ አክሱምና ላሊበላ ቦይ፤ገዳማት፣ ደብሮች፣ ውቅር ድንጋዮች እና ግንባታዎች አልፎም በግብፅ ሄሮግሎፊክ ፊደላችን በድንጋዮቻቸው ላይ የስልጣኔን ሥር ቀዳጅ ኪነ ጥበባቸውን ይነቅሱ ነበር።

ላለፈው የአገራችን ታሪክ ታዲያ ወጣቱ የራሱ ድርሻ ነበረው ማለት ነው። ወጣትነት ሀይል ነው ሁሉን የማወቅ፣ የመንካትና የመቅመስ ፍላጎት በእጅጉ እንደ ሞተር የሚንርበት ልከኛ የዕድሜ ክፍል ቢኖር ወጣት ዕድሜ ነው። ወጣት ዛሬ በፊልም የተመለከተው ድንቅ ተዋናይ፣ያነበበውን ዝነኛ ገፀ ባሕሪ፣ አመራር የሰመረለትን ርቱእ የፖለቲካ መሪ፣ ተመልካች ያወደሰውን ድንቅ ስፖርተኛ ወዘተ… መሆን እንደተመለከተው ቢሻ የዛኑ ዕለት እጅግ የሚደንቅ አይደለም፤ በእርግጥ ባለ ውጤቱ እዚህ ለመድረስ ከከፈለው ረጅም የትግል መንገድ ይልቅ ዛሬ የሆነውን ይፈልጋል። በዚህ ጊዜ ነው ስሜቱን ሊገዛለት የሚችል የሰከነ እገዛ፣ ድጋፍ፣ ምክርና አመራር የሚያስፈልገው።

በአሁኑ ሰዓት የአገራችን ወጣት ሕብረተሰብ ፖለቲካን በተመለከተ ለመወያየት ሆነ ለማነጋገር ሲሞከር ተስፋ የመቁረጥ፣ የመሰላቸት ወይም የመቆጣት ሁኔታዎች የሚበዛበት ጊዜ ላይ እንድንደርስ ሆነናል። በእርግጥ የአገራችንን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ስንመለከት ከንጉሳዊ አገዛዝ ጀምሮ እስከ አሁን የወጣት ተሰሚነትና ተቀባይነት ኢምንት ነበር አሁንም ነው። በአብዛኛው ማለት ይቻላል የፖለቲካው ድምዳሜ ወይም ውሳኔዎች የሚካሄደው ከጎልማሳውና አዛውንቱ ክፍል ነበር። የፖለቲካ አካሄዱ አንድ ዓይነት ወጥ ነበር፤ ይህም ከላይ ወደ ታች ክፍል የማውረድ ነበር። በንጉሳዊ አገዛዝ ወቅት ለውጥ ይምጣ መሬት ላራሹ ብሎ ድምፅ ማሰማት የጀመረው የወጣት ክፍል ነበር ሆኖም አድማጭ አላገኘም፤ በደርግም ጊዜ ወጣቱ የፖለቲካው ተሳትፎው ባላመነበትና በማይፈልገው የፖለቲካ ርዮተ-ዓለም ወታደርነት ከመቀጠር ያለፈ አልነበረም ስርዓቱ ከዚህም የዘለለ የፖለቲካ አካሄድ እንዲያደርግ ፍጹም አልፈቀደለትም፡ ለዚህም በቀይ ሽብር ዘመቻ ሰለባ የሆኑ ወጣቶች በቂ አብነት ናቸው። ምንም እንኳን ያሰበውን አላማ ውጤታማ ማድረግ ባይችልም በዚህ ጊዜ የነበረው የወጣት ክፍል እስከ አሁን ከታዩት



EthioLion.com

Ethiopia Will Prevail!

የወጣት ክፍል ጠንካራው ክፍል ነበር። የአሁኑን የወጣቱ ክፍል ፖለቲካ ተሳትፎ ደግሞ ከላይ ካየናቸው ችግሮች ተመሳሳይ ሁኔታ እያጋጠማቸው ነው። ዓለም በተቀየረበት ዲሞክራሲ እንኳን ከኋላችን የነበሩትና ትናንት የተወለዱት አንዳንድ የአፍሪካ አገራት ማራመድ በጀመሩበት ሰዓት በአገራችን ግን በተቃራኔው አንድ ወጥ የሆነ ኢ-ዲሞክራሲያዊ አካሄድ በሚያራምድ በአንድ ፖርቲ ብቻ በሚመራ የጭቆና፣ የአፈና የጨለማ ሁኔታ የሚታይበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ከዚህም በተጨማሪ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ዝብርቅርቅና አሰልቺ መልክ የያዘበት ሁኔታ አለ። ሀቀኛውን ከአስመሳዩ ለመለየት፣ ጠንካራውን ከደካማው ለመምረጥ ወጣቱ የሚቸገርበት ጊዜ ላይ ይገኛል። በሌላ በኩል ለሕዝብና ለአገር መፍትሔ አለን እያሉ የሚመጡትም ድርጅቶች የግል ጥቅማቸውንና ድብቅ ፍላጎታቸውን በመሸሸግና ለእውነት ትግል የቆሙለት በመምሰል በየሰላማዊ ሰልፍና በየመንደሩ እንደ ሰባ ሚዳቋ ለወያኔ ጥይት እያስቆሉት ፍሬውን የማያየውን አላስፈላጊ መስዋዕትነት ሲያስከፍሉት፡ እርም ለአገር የጋራ ትግል፣ እርም ለኢትዮጵያ ፖለቲካ እያለ እራሱን ከትግል ተሳትፎ እንዲያገል ይገደዳል። ይህም ቢሆን ግን በአሁኑ ሰዓት ወጣቱ በተፈለገውና በአጥጋቢ ሁኔታ ፖለቲካው  የራሴ ጉዳይ ብሎ አልያዘውም ይህም ደግሞ ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም በየትኛውም ዓለም ፈተና የሌለው የፖለቲካ አካሄድ ስለሌለ፤ በዚህም አለ በዛ ወጣቱ ምክንያት ሳያበዛ ወደ ፖለቲካ መምጣት ግዴታው መሆኑ መረዳት ያለበት ጊዜ አሁን ና አሁን ነው። ይህ ካልሆነ የምናስበውና የምንናፍቀውን የተስተካከለች አገር ለመረከብ እንቅፋት መሆናችን ነውና።

ዋናው ነጥብ የአሁኑ ወጣት ወደ ፖለቲካው መድረክ ማምጣት አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነው። የወጣቱንም የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ ከተፈለገ ግን እንቅፋት የሆኑበት ከ ብዙ በጥቂቱ ችግሮችና መፍቴሔዎች ማየት አስፈላጊ ነው። የአገራችን ፖለቲካን በእጅጉ አስፈሪ ምስል ሰጥተን ጨዋነታችን ከፖለቲካው በራቅነው መጠን መለካታችን አገራችንን ለቀማኛና በዝባዥ አሳልፈን ከመስጠታችን ባሻገር የወደፊቷዋን ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ከፍትህና ከዲሞክራሴ እንቅስቃሴ ውጪ እያደረግናት መሆኑን መርሳት የለብንም። በፖለቲካ ውስጥ እንደ ጋሪ ፈረስ እየተነዳ ይመራል እንጂ ማንም ዜጋ ያለ ፖለቲካ መኖር ፈጽሞ አይችልም። እርሱ ፖለቲካን ይርቃል እንጂ ፖለቲካ እርሱን አይርቀውም በአንድም አለ በሌላ የስርዓቱ ተገዥ ነውና፤ የሚጠቀምበት ፍርድ ቤት፣ የሕዝብ ተቋማት፣ የሚከተለው የንግድ ሲስተም የፖለቲካ ተፅዕኖ እንዳለባቸው እየታወቀ ጆሮ ዳባ ልበስ አካሔድ አገርንም ህብረተሰብም የሚጎዳ ነው። ፖለቲካውን እንድንጠየፈው ያደረጉትን የትናንት በይበልጥ የዛሬዎቹ አገዛዝ ቢሆኑም ዛሬ ለሚታየው የወጣቱ ንቁ ተሳትፎ አለመኖርና የፖለቲካውን ሥራ የመሰላቸት ሁኔታ መታየት ችግሮችን ከሁለቱም አንፃር ፈርጅ ማየት ተገቢ ነው።

<u>ከወጣቱ አንፃር</u>፡- ስንነሳ ወጣቱ ፖለቲካውን በርቀት ማየት የሌለበት ሲሆን «የማይቀርብህን እንግዳ አጥብቀህ ሳመው» እንደተባለውና ከላይ እንደተጠቀሰው  ወጣቱ በፖለቲካ ካልተረማመደ ምንግዜም ድብቅ ወይም ጥላ ሆኖ ከመቅረት ውጭ ምንም አማራጭ የለውም፤ ምክንያቱም የሚገለገልበት የፍትህ አገልግሎት፣ የትምህርት ተቋማት፣ የንግድ ቦታ፣ የሚያርሰው መሬት ወዘተ… በፖለቲካው ስርዓት አገዛዝ ውስጥ የተካተተ ነውና።

ሌላው መሰመር ያለበት ጉዳይ ወጣቱ ታጋሽ መሆን ይኖርበታል። « ሺ እርምጃ በአንድ ይጀመራል» እንደሚባለው የአንድን አገር የተስተካከለ የዲሞክራሲ አካሔድ ለመፍጠር ዓመታት ሊወስድ እንደሚችል መገንዘብ አለበት። በአሁኑ ሰዓት ደቡብ አፍሪካን በጥምር መንግሥት በአብዛኛው 2/3 የፖለቲካ ስልጣን በመያዝ በመምራት ላይ ያለው ANC (African National congress) ይህም እድል ያገኘው ከ50 ና 60 ዓመታት በላይ ከረጅምና አስቸጋሪ መስዋትነት በኃላ ነው። ታዲያ ይህ ድርጅት በዚህ ረጅም የፖለቲካ



Ethiopia Will Prevail!

እንቅስቃሴው የተጠቀመው ጉዳዮች ብዙ ነበር፤ ይህም የጠራ የፖለቲካና ሶሻል ይሁን ሌላውን አካሔድ ያጠናበት ፣ የፈተሸበትና የመከረበት ሁኔታ ነበር፤ ስለዚህም በአሁኑ ሰአት የአብላጫውን ሕዝብ ተቀባይነት በማግኘት አገር እየመራ ያለው። ወጣቱ ከANC ድርጅት መማር ያለበት የአንድን አገር ሙሉ የፖለቲካ ይዞታ ለመቀየርና ለማስተካከል ረጅምና አሰልቺ ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል መገንዘብ እንዲሁም በትዕግሥት በፖለቲካው እንቅስቃሴ የበኩሉን በመወጣት መሰንበት እንዳለበት ነው።

<u>በፖለቲካው ውስጥ በንቃት ካሉት አንፃር</u> ሲታይ ወጣቱን በአዲስ አቀራረብ በዘመናዊ ሁኔታ የመቅረብ ሁኔታ መፈጠር ይጠበቅባቸዋል። የትናንቱ ታሪክ ና አካሔድ ልምድ ከመሆኑ ውጭ ምንም ቢሆን ምንም አለም እየተቀየረች ነውና፤ የትናንቱን ልምድ ከአሁኑ ለውጥ በየአቅጣጫው ማቀናበር ሲኖርባቸው፤ የቀደሙት ተሞክሮአቸውን በመጠቀም ድክመታቸውን በማስወገድ ጠንካራውን በተገቢ ሁኔታ በመንቀስ አዲስና ውብ የሆኑ ዘዴዎችን እየነደፉ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዎል።

ወጣ ወጣ ማለት የጀመሩ ወጣት ፖለቲከኞች ስህተታቸውን ከማጉላት ይበልጥ ጠንካራ ጎናቸውን በማገዝ ብዙ መንገድ እንዲሔዱ ማበረታታት ተገቢ ነው። ወደድንም ጠላንም ከ30 ዓመት በፊት የነበረው ፖለቲካና የፖለቲካ አካሔድ ከዚህ ዘመን የፖለቲካ አካሔድ ጋር ሙሉ በሙሉ መሄድ አይችልም።

ጠቅለል ባለ መልኩ የዚህ ጽሁፍ ዋና ዓላማ በአጋጣሚ ሆነ በፈለገውም ሁኔታ ወደ ፖለቲካ ተሳትፎ የገባውም ያልገባውም ተሳትፎውን እንደሌላው የአለም ክፍል የግሉን ሆነ እንዲሁም የህብርተሰቡን የአገሩንም በአጠቃላይ የሁሉንም ሁኔታ የሚፈታበት መሳርያ አድርጎ የፖለቲካ እንቅስቃሴን በንቃትና በሰፊው እንዲሳተፍ ለመገፋፋት ነው። ወጣቱ አዲስ፣ ማራኪ፣ ቀላልና ዘመናዊ ያልተንዛዛ የፖለቲካ አካሄድ ይስበዋል። ወጣትን ምንጊዜም በውይይትና በሐሳብ አሸንፈን ወደሱ ካልቀረብን በሃይልና በማስፈራራት ያላመነበትን ወይም ግፊት የበዛበትን አካሄድ ፈጽሞ አይቀበልም፤ ቅን ሃስብ ና አካሂድ አፋና በፍፁም አይመቸውም። ወጣት ባብዛኛው የግል ነፃነትን ያንፀባርቃል፣ ዋናው ነጥብ የግል ነፃነቱ እንደተጠበቀ ቅንነትና ግልፅነት በተሞላ አካሔድ ከቀረቡት አንድ ጥሩ የአገር አመለካከት ያለውን ወጣት አይደለም የተሳሳተ አመለካከት ያለውንም የማዳን ሥራ መሥራት ይቻላል።

በተመሳሳይ በወጣቱ አካባቢ የምንቀርብበት ቋንቋ አጠቃቀም ማየትም አስፈላጊ ነው። ወጣት ግልጽና ተስፋ ሰጪ የፖለቲካ ቃላት በይበልጥ ይስበዋል፤ በአጠቃላይ በአንፃሩ ጦርኝነት፣ ዘረኝነት፣ ጎሰኝነት፣ በምንም መልኩ አይቀበለውም። የፖለቲካ ሃሳብ ልዩነት በውይይትና በስምምነት፤ የዘር ልዩነትን በአገራዊነት፣ በዜግነት፣ በእኩልነት እያመዛዘንን ማስማማት እንደሚቻል በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ልናስረዳው ይገባል። ለምሳሌ ያህል ባለፈው በአሜሪካ በተደረገው ምርጫ ኦባማ የተጠቀመበትን የምርጫ ስልት ማየት ይቻላል፤ እንደሚታወቀው ከኦባማ በፊት አሜሪካን ለ8 አሰልቺ ዓመታት የመሩት ሪብፐሊካን ነበሩ በእነዚህ ዓመታት በአሜሪካና በመላው ዓለም የተለያዩ ደካማ የፖለቲካ አመራር ውጤት የሆኑ ችግሮች ተከስተው ነበር (የኢኮኖሚ ቀውስ፣ የሽብርተኞች ችግር ወዘተ…) ብልጣ ብልጡ ኦባማ ከዘር ከቀለምና ሌሎች ነገሮች በዋንኛነት የተጠቀመበት ዘዴ ወጣቱን ክፍል በልዩ ሁኔታ በቀላልና ግልጽ በሚያሳትፍ ሁኔታ ወጣቱን ማንቀሳቀስ ነበር፤ ያን ሁሉ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ነፃ የምርጫ ቀስቃሽና አነሳሽ ወጣቶች ወደ ዲሞክራትስ የቀረቡበት ምክንያት በጣም ግልጽ ነበር። ይህም ረፐብሊካን የአገሪቱን የፖለቲካ እንቅስቃሴና አካሄድ የሀብታሞች፤ የአረጋውያን ባለፀጎች፣ የኢምፐሪያሊስት እንዲሁም በአብዛኛው የነጭ የበላይነት በሚያሳይ የፖለቲካ አመራር እንደሆነ ያስረዳው ኦባማ ለወጣቱ በግልፅ፣ በዘመናዊ፣ በቀላልና ማራኪ አቀራረብ ነበር ሌላ ምንም ሚስጥር



Ethiopia Will Prevail!

አልነበርም። እናም ይህ አቀራርብ የሳበው ወጣቱ ድምጽ በመስጠት ይሁን በማነሳሳት የሰራው ታሪክ በአሜሪካ ምርጫ ልዩ ታሪክ ነበር።

ወደ አገራችን ስንመለስ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ በረጅምና ፅኑ የፖለቲካ ትግሉ የሚታወቀው ኢሕአፖ በአፍሪካ በዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲነቱ በዲሞክራሲያዊ መርሐ ግብር ፈር ቀዳጅነት፤ ወጣትነትን እያማከለ ከቀደምቶቹ ወጣት ሊግ እስከ ዛሬዎቹ ኢሕአፖ ወክንድ ድረስ ትግሉን መዘርጋቱ ሊወደስ የሚገባ ነው። ድርጅቱ የሙሑሮች፣ የመሪዎች፣ የፀሐፊዎች ወዘተ… የእውቀት ሀብታም ድርጅት ነው። ኢሕአፖ በፖለቲካውም፣ በሶሻልም፣ በሃይማኖቱም ወዘተ… የሚከተለው ፖሊሲ ግልጽና የጠራ ነው፤ አገርንም የመምራት አቅምና ብቃት አለው። የዘመኑም ወጣት የወደፊቱ የአገሪቱ ዕጣ ፈንታ ወሳኞች በመሆናቸው ከሁሉም ነገር በፊት አገር ይቀድማልና በሙሉ ፍላጎትና አቅም በፈቀደው መጠን በድርጅት በመታቀፍ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድርግ የዜግነት ግዴታ መሆኑን በመገንዘብ ወደ ፖለቲካ ሊገቡ ሊታገሉ ይገባል።

<u>መደምደሚያ፣</u> የፅሁፌን ርእስ የመረጥኩበት ምክንያት ልግለፅ፣ ኢሕአፓ ከጥንትም ጀምሮ በወጣቶችና በሴቶች ትግል የሚያምን እንዲሁም ወጣቶች ለአገራችን ኢትዮጵያ ተተኪ ትውልድና መጥፎውን አገዛዝ የሚለውጡ ታሪክ ቀያሪ ናቸው ብሎ ሰለሚያምን፤ኢሕአፖ ወክንድም የትግልን ሁኔታ ጥንት ከነበሩት የኢሕአፓ አመራር ከታሪካቸው በመማር እንዲሁም እስከ አሁን ድረስ ሰለቸን ደከመን ሳይሉ እየሰሩ እየደከሙ እንዳሉ የተገነዘቡ፤ ያሁኑ ወጣት የነሱን ዓርዓያ ተከትሎ በትግሉ ጎራ ተሰልፎ ሰለሚገኝ፣ በአምባገነኖች ተጠርንፋ የተያዘችው አገራችን ኢትዮጵያና ህዝቦቿ አሁን ካለችበት ጭቆና ነፃ ማውጣት አለብን በማለት በመታገል ላይ ስለሚገኝ ነው። ይህም በመሆኑ ትግሉ የተሳካ ና የሰመረ እንዲሆን በየአቅጣጫው ያለው ወጣት እጅ ለ እጅ ተያይዞ አገሩን ነፃ ለማውጣት ይነሳ!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!!!!!!

EthioLion.Com